# ሽግግር፦ ቀጣዩ እርምጃ

## ልጁ ሶስት ዓመቱ ሲሞላው ምንድን ነው የሚፈጠረው?



*በ Individuals With Disabilities Education Act (የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ፣ IDEA) ክፍል ሐ መሠረት ከቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ወደ ሽግግር የሚያስኬድ መመሪያ።*

በ Washington Department of Children, Youth, and Families, Early Support for Infants and Toddlers (የWashington ስቴት ዲፓርትመንት የህፃናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች፣ የህፃናት እና ታዳጊዎች ቅድመ ድጋፍ ፕሮግራም) የተደገፈ።

Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

# ሽግግር ምንድን ነው?

ልጅዎ ሶስት አመት ሲሞላው የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶቹ ያበቃሉ እናም አዳዲስ አገልግሎቶች እና ድጋፎች ሊገኙ ይችላሉ። ይህ የለውጥ(ሽግግር) ሂደት በህይወትዎ በሙሉ ለልጅዎ እና ለቤተሰብዎ ከሚከሰቱት ብዙ ሽግግሮች ውስጥ አንዱ ነው።

የልጅዎ ሶስተኛ የልደት ቀን ከስድስት እስከ ዘጠኝ ወራት ቀደም ብሎ ከ family resources coordinator (ቤተሰብዎ ግብዓት አስተባባሪ፣ FRC) እና ቡድንዎ ጋር ወደ ቅድመ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ወይም ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶች እና ድጋፎች ለመሸጋገር እቅድ ማውጣቱን ይጀምራሉ። ቤተሰቦች እና አገልግሎት ሰጪዎች ይህንን ሂደት አብረው ወደ ሽግግር ስብሰባ በሚያመራ ጉዞ ይሄዳሉ።

# የሽግግር ስብሰባው ዓላማ ምንድን ነው?

የ Individualized Family Service Plan (ግላዊ የሆነ ቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ፣ IFSP) ስብሰባ ወቅት፣ በሽግግሩ ሂደት ውስጥ እርስዎን ለመምራት በእርስዎ እና በቅድመ ጣልቃ ገብነት ቡድንዎ የጽሁፍ ሽግግር እቅድ ይዘጋጃል።

Individuals with Disabilities Education Act (የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግ፣ IDEA) ክፍል ሐ ልጅዎ ሶስተኛ ዓመቱን ከመያዙ በፊት ለሽግግር የጽሁፍ እቅድ ያስፈልገዋል።

# ለሽግግር ማቀድ ያለብን መቼ ነው?

## ከልጅዎ ልደት በፊት ከሶስት እስከ ዘጠኝ ወራት፦

የሽግግር እድቅ ይጀምራል። በሦስት ዓመታቸው የልጅዎን ሽግግር ማቀድ ለመጀመር የእርስዎ FRC በእርስዎ እና በትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ወይም በሌሎች ማህበረሰብ-ተኮር ፕሮግራሞች መካከል ግንኙነትን ያመቻቻል።

## የልጅዎ ሶስተኛ የልደት ቀን ቢያንስ ከሶስት ወር በፊት የሽግግር እቅድ ስብሰባ ይካሄዳል:-

እንደ የስብሰባው አካል ከትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት(አውራጃ) ተወካይ ጋር ይገናኛሉ። ልጅዎ ለቅድመ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ መሆኑን ለማወቅ ምን እንደሚሆን ያስረዳሉ።

በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት እንደተወሰነው ልጅዎ ለቅድመ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ ከሆነ፣ አገልግሎቶች በ Individualized Education Program (የግል የትምህርት ፕሮግራም፣ IEP) በኩል ይሰጣሉ።

የመዋለ ሕጻናት ልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን መቀበል ካልፈለጉ፣ ከትምህርት ቤት ዲስትሪክት ተወካይ ጋር ስብሰባ አይደረግም።

# የሽግግር እቅድ ምንድን ነው?

የሽግግር እቅድ ልጅዎ እና ቤተሰብዎ በሶስት ዓመታቸው ከቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ሲወጡ እርስዎ፣ የእርስዎ FRC እና የቅድመ ጣልቃ ገብነት ቡድንዎ እንዴት እንደሚረዱ ይለያል። እቅዱ ልጅዎ በአካባቢዎ በሚገኝ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ቅድመ ትምህርት ልዩ ትምህርት ፕሮግራም ወይም ሌላ ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ አገልግሎቶች ሲገባ ወይም ድጋፎችን እና አገልግሎቶችን ሲተው ምን አይነት ድጋፎችን፣ እርምጃዎችን እና አገልግሎቶችን እንደሚያስፈልግ ይገልጻል።

# ለልጄ ቀጣይ ላይ ያለው ምንድን ነው?

## የልጄን የሽግግር እቅድ ማውጣት፦

እርስዎ እና የቅድመ ጣልቃ ገብነት ቡድኖች እቅዱን ለማውጣት በጋራ ይሰራሉ። ቡድኑ እርስዎን፣ የእርስዎን FRC፣ አሁን ከልጅዎ ጋር የሚሰሩ ሰዎችን፣ እርስዎ ሊሳተፉባቸው የሚፈልጓቸው ሌሎች ግለሰቦች እና ወደፊት ከልጅዎ ጋር ሊሳተፉ የሚችሉ ሰዎችን በውስጡ ያካትታል። ቡድኑ የልጅዎን አፈጻጸም እና ፍላጎቶች ይመለከታል። FRC የዚህን የሽግግር እቅድ አዋጣት ያቀናጃል።

## ከሽግግር በኋላ በሶስተኛ እድሜው ምን አይነት አገልግሎቶች ሊገኙ ይችላሉ?

ይህም የሚወሰነው ልጅዎ የመዋለ ሕጻናት ልዩ ትምህርት አገልግሎት ያስፈልገዋል ወይ በሚለው ላይ ነው። የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት ልጅዎ ለቅድመ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ መሆኑን ዉሳኔውን ይሰጣል። ልጅዎ ብቁ ከሆነ፣ እንደ የማህበረሰብ ፕሮግራም፣ Head Start፣ Early Childhood Education and Assistance Program (የቅድመ ልጅነት ትምህርት እና የእርዳታ ፕሮግራም፣ ECEAP) ወይም በት/ቤት ላይ የተመሰረተ፣ የቅድመ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርት ፕሮግራም የመሳሰሉ የተለያዩ የአገልግሎት ቅንብር አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ። የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በ IEP ብኩል ነው የሚቀርቡት። FRC የሽግግር እቅድ ስብሰባን ያስተባብራል። የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የልጅዎን IEP ለማዳበር ስብሰባ ያዘጋጃል።

FRCዎ ወደ IEP ስብሰባ እንዲጋበዝ መጠየቅ ይችላሉ። ለ IEP ስብሰባ ድጋፍ ለማግኘት ጓደኛ፣ የቤተሰብ አባል ወይም ሌላ የመረጡት የማህበረሰብ አባል ይዘው መምጣት ይችላሉ። Developmental Disabilities Administration (የእድገት አካል ጉዳተኞች አስተዳደር፣ DDA) ጉዳይ አስተዳዳሪ ካለዎት ወይም Children with Special Health Care Needs (ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ያላቸው ልጆች፣ CSHCN) አስተባባሪ ካለዎት እነሱንም መጋበዝ ይችላሉ። የIEP ስብሰባ ከልጅዎ ሶስተኛ ልደት በፊት መከሰት አለበት እና IEP በልጅዎ ሶስተኛ የልደት ቀን ውስጥ መሆን አለበት። IEP ስብሰባዎች በየዓመቱ ነው የሚታቀዱት ሆኖም፣ እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ስለልጅዎ ፕሮግራም መወያየት እንደሚያስፈልግ በተሰማዎት በማንኛውም ጊዜ የ IEP ስብሰባ መጠየቅ ይችላሉ።

## የኔ ልጅ ለቅድመ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ ካልሆነ ምን ይሆናል?

ልጅዎ ለቅድመ ትምህርት ቤት ልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ ካልሆነ፣ እንደ Head Start፣ ECEAP ወይም ሌሎች የማህበረሰብ ፕሮግራሞች ያሉ ለልጅዎ ሊገኙ የሚችሉ ሌሎች አማራጮችን ለመለየት የእርስዎ FRC ከእርስዎ ጋር ይሰራል።

## በሽግግር ሂደቱ የእኛ ድርሻ ምንድን ነው?

### ልጅዎ እና ቤተሰብዎ ለስላሳ ሽግግር እንዲያደርጉ እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ላይ ጠቃሚ ምክሮች፡-

- ለልጅዎ ምን እንደሚፈልጉ በመናገር በስብሰባዎች ላይ ይሳተፉ።
- በስብሰባው ላይ ማስታወሻ ይያዙ።
- ያሉትን ሃብቶች እና አገልግሎቶች ይወቁ።
- ስለልጅዎ እንቅስቃሴዎች እና ፍላጎቶች ማስታወሻ ደብተር ያስቀምጡ። የልጅዎን የልደት የምስክር ወረቀት፣ የክትባት መዝገብ፣ የበሽታን የመከላከል ህክምና(ክትባት) ዘገባዎች፣ ፎቶግራፎች፣ ግምገማዎች፣ ምዘናዎች እና ያለፈውን IFSP በውስጡ ያካትቱ። የልጅችዎ የፎቶ እውነታዎችን እና መረጃዎችን ግላዊ ለማድረግ ያገለግላሉ።
- ለልጅዎ ለመሚገት ጠቃሚ ሊሆን የሚችል ምን አለ? እሷን/የሱ ፍላጎቶችን በደንብ ያውቃሉ። ከልጅዎ ምን እንደሚጠብቁ ይወቁ እና እነዚያን አገልግሎቶች ለልጅዎ ለማግኘት ከትምህርት ክልሉ እና ከ IEP ቡድን ጋር አብረው ይስሩ።

## ከሽግግር በኋላ የእኔ ቀጣዩ ደረጃዎች ምንድን ናቸው?

በዲስትሪክትዎ ውስጥ የቤተሰብ ድጋፍ ቡድን፣ የአካባቢ Parent Teacher Student Association (የወላጅ መምህር ተማሪዎች ማህበር፣ PTSA) ወይም Special Education Parent Advisory Council (የልዩ ትምህርት የወላጅ አማካሪ ምክር ቤት፣ SEPAC) ካለ ይጠይቁ። የሚያሳስብዎት ነገር ካለ ሊረዳዎ የሚችል የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኛ፣ ማህበራዊ ሰራተኛ ወይም የትምህርት ቤት የስነ-ልቦና ባለሙያ እንዳለው ድስትሪክቱን ይጠይቁ። ቤተሰብዎ በሽግግሩ ሂደት ውስጥ ሲያልፍ እርስዎ፣ ወላጅ እንደመሆንዎ፣ ለራስዎ እና ለልጅዎ ድጋፍ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ልብ ይበሉ።

## ሌላ ማወቅ ያለብን ምን አይነት መረጃ አለ?

ልጅዎ በአሁኑ ጊዜ ከ DDA አገልግሎት ለማግኘት ብቁ ከሆነ፣ ልጅዎ አራት ዓመት ሳይሞላው ለአገልግሎቶች ብቁነት እንደገና መወሰን አለበት። በዚህ የሽግግር ሂደት ውስጥ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ግምገማዎችን፣ የሽግግር መረጃን እና የትምህርት ቤቱን የግምገማ ሪፖርት ከ DDA ጋር ማጋራት አስፈላጊ ነው። **DDA ይህንን መረጃ ለመልቀቅ ፈቃድዎ ከት/ቤት ዲስትሪክት በሽግግር እቅድ ስብሰባው ላይ ሊገኝ ይችላል።** የልጅዎን ቀጣይነት ብቁነት ለመወሰን መረጃው ካልደረሰ፣ ልጅዎ በአራት ዓመቱ ከ DDA አገልግሎቶች ይወጣል።

## እገዛ ስፈልግ ወይም ተጨማሪ መረጃ ስፈልግ ከየት ማግኘት እችላለው?



Department of Children, Youth & Families Early Support for Infants and Toddlers (የህፃናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች ቅድመ ድጋፍ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች፣ ESIT) ፕሮግራም የ IDEA ክፍል C የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን በክልል አቀፋዊ ስርዓት ይመራል።

**esit@dcyf.wa.gov**
**www.dcyf.wa.gov**

ለበለጠ መረጃ እና ለ family resource coordinator (የቤተሰብ ሃብቶች አስተባባሪ፣ FRC) ሪፈር ለማግኘት በአካባቢዎ ላለው የ FRC ስም Help Me Grow Washingtonን ያግኙ።

1-800-322-2588

በ Kindering Center(በመዋለ ሕጻናት ማዕከል) ውስጥ የ Washington ግዛት የአባቶች ኔትዎርክ። ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልጆች ላሏቸው ሁሉም ወንዶች እና ቤተሰቦቻቸው ጠበቃ እና ድጋፍ እና ግብዓቶችን ይሰጣል።

(425) 653-4286
**www.fathersnetwork.org**

PAVE የአካል ጉዳተኛ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች እርዳታ እየሰጠ ያለ የወላጅ ማሰልጠኛ እና የመረጃ ማዕከል ነው።

1-800-572-7368 (800-5 PARENT)
**www.wapave.org**

የ Washington ግዛት ወላጅ ለወላጅ የአካል ጉዳተኛ ልጆች ወይም የእድገት መዘግየቶች ያለባቸው ልጆች ላላቸው ወላጆች ስሜታዊ ድጋፍ እና መረጃ የሚሰጥ በስቴት አቀፍ የወላጅ መረብ ነው።

1-800-821-5927
**www.arcwa.org/parent-to-parent**

Arc of Washington State (የዋሽንግተን ስቴት አርክ) ትምህርትን፣ ጤናን፣ ራስን መቻልን፣ ራስን መደገፍን፣ ማካተትን፣ እና የእድገት እክል ያለባቸውን ግለሰቦች እና ቤተሰቦቻቸውን ምርጫ ያበረታታል።

1-888-754-8798
**www.arcwa.org**

Office of Superintendent of Public Instruction (የህዝብ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ) ልዩ ትምህርትን እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚቀበሉ ልጆች ላላቸው ወላጆች ጠቃሚ የሆነ ድር ገጽ **www.k12.wa.us/specialEd/families/default.aspx** አለው።

በ **Washington State Department of Children, Youth & Families (የዋሽንግተን ስቴት የህፃናት፣ ወጣቶች እና ቤተሰቦች ዲፓርትመንት)** ለጨቅላ ህፃናት እና ታዳጊ ህፃናት የሚሰጥ የቅድመ ድጋፍ።

PO Box 40970
Olympia WA 98504-0970
**esit@dcyf.wa.gov**
**www.dcyf.wa.gov/services/child-development-supports/esit**

*ማዳላት በሁሉም ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች የተከለከለ ነው። ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በእምነት፣ በብሔር፣ በጾታ፣ በእድሜ ወይም በአካል ጉዳተኝነት መገለል የለበትም።*

*የዚህን ሰነድ በአማራጭ መልክ ወይም ቋንቋ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎን የ DCYF Constituent Relations (የ DCYF የህብረት ግንኙነቶችን ያነጋግሩ) (1-800-723-4831 | 360-902-8060, **ConstRelations@dcyf.wa.gov**).*

DCYF PUBLICATION FS_0004 | DEL 11-013 AM (07-2023) Ahmaric